# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 133 ህዳር 23 ቀን 2003 ገጽ 1


**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት አመራር በአንድ ብሔር ተወላጆች ቁጥጥር ስር መሆኑ ተጋለጠ

በዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ሙሉ ቁጥጥር ስር ያለው የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት አመራር በትግራይ ተወላጆች ብቻ ተይዞ እንዳለ በአገዛዙ ውስጥ ያሉ የግንቦት 7 ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ያስተላለፉት መረጃ አመልክቷል።

ግንቦት 7 ከዚህ ቀደም ባወጣቸው በርካታ ሪፖርቶች ቁልፍ የመንግስት የስልጣን መቀመጫዎች ከአንድ ብሄር በተመረጡ ጥቂቶች ቁጥጥር ስር እንዳለ እና በተለይም በመከላከያ ውስጥ ካሉት 60 ቁልፍ መቀመጫዎች ውስጥ 57ቱ በትግራይ ተወላጆች የተያዙ እንደሆኑ ማጋለጡ ይታወሳል።

የአዲስ አበባን ማረሚያ ቤት በተመለከተ የደረሰን መረጃ የአመራር አባላቱን ስም ዝርዝር፤ ተቋሙ የተዘፈቀበትን ሙስና፤ በእስረኞች ላይ የሚፈጸመውን ግፍ እና ኢ-ሰብአዊ ድርጊት፤ እንዲሁም የማረሚያ ቤቶቹን አስከፊ ሁኔታ በዝርዝር ያስረዳል።

የመረጃው አቀባዮች አመራሩ በዘር የተዋቀረበትን ምክንያት ሲገልጹ፤ ወያኔ በህግ የበላይነት የሚያምን ቡድን ባለመሆኑ ያሻውን ግፍ እና ዘረፋ ሁሉ ያለ ጠያቂ ለማከናወን እንዲያመቸው ነው ካሉ በኋላ፤ ለዚህ ደግሞ ሌላውን የህብረተሰብ ክፍል አያምንም ብለዋል።

በተያያዘ ዜና ይህ በዘር ላይ የተደራጀ አመራር፣ በአድስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ ማረሚያ ቤቶች ዘግናኝ እና ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶችን እየፈጸመ እንደሆነ የመረጃ ምንጮቻችን አክለው ገልጸዋል ። ማረሚያ ቤቶቹ እንደ አንድ መንግስት ተቋም ሳይሆን እንደ ማፊያ ድርጅት በወንጀለኝነት ከአንድ ብሄረሰብ በተሰባሰቡጥቅም አሳዳጆች እና በወንዝ ልጅነት ባሰለፉዋቸው(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ አገዛዝ በአራት የትጥቅ ቡድኖች ጥምረት መመስረት ላይ ያወጣው መግለጫ የባለስልጣናቱን መረበሽ አንጸባርቋል ተባለ

የዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በቅርቡ በተመሰረተው የትጥቅ ቡድኖች ጥምረት ላይ ያወጣው መግለጫ በርካቶችን ግራ አጋብቶ የሰነበተ ሲሆን፤ አንድ የፖለቲካ ተንታኝ በአገዛዙ ዘንድ ያለ ያለመረጋጋት ነጸብራቅ ነው ብለውታል።

"ጥምረት የኢትዮጵያውያን ለዴሞክራሲ ለውጥ" የተባለ እና አራት የትጥቅ ቡድኖችን ያካተተ ህብረት መፈጠሩን የምስረታውን መግለጫ ጠቅሶ ዘገባውን ያስተላለፈው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት - ኢሳት - የጥምረቱ መስራቾች:- "የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ የቤኒሻንጉል ህዝብ ነፃነት ንቅናቄ፣ የጋምቤላ ህዝብ ነፃነት ንቅናቄ እና የኢትዮጵያ ህዝብ የፍትህና እኩልነት ግንባር" መሆናቸውን ገልጾ ነበር።

ዘግይቶ መግለጫ ያወጣው የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በአንድ ጎን ቡድኖቹን የወደቁ ብሎ ሲያጠቃ፤ ይህንኑ ሲናገር ግን በቁጣ የተሞላ ሶስት ገጽ ጽሁፍ ማውጣት ለምን እንዳስፈለገው ግልጽ አላደረገም። እርስ በርሱ የሚጣረሰው ጽሁፍ ጨምሮም፤ እነዚህ የሞቱ እንደሆኑ የተነገረን ቡድኖች በአገዛዙ ላይ የደህንነት ችግር እንደሚፈጥሩ ይገልጻል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የአማራ ክልል ገበሬዎች በትምህርት ጥራት ጉድለት ላይ ቅሬታ አሰሙ

የአማራን ህዝብ ለዘረኛው የወያኔ ቡድን በማስገዛት ስራ የተመደቡት የብአዴን ባለስልጣናት በቅርቡ በጎንደር ባካሄዱት ስብሰባ ላይ ባልገመቱት መንገድ ከአካባቢው ገበሬዎች በጥያቄ መጣደፋቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

የስብሰባው ተሳታፊዎች ልጆቻቸው በአግባቡ እየተማሩ እንዳልሆነ በማንሳት ምሬት ማሰማታቸው ታውቋል። ገበሬዎቹ፥ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት የሚልኩት በቂ ትምህርት አግኝተው ስራ በመያዝ ህይወታቸው እንዲለወጥ እና የራሳቸውም ሸክም እንዲቀንስ ቢሆንም፤ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ የተማሩት ልጆች ደብዳቤ እና ማመልከቻ እንኳን ሊጽፉልን የሚችሉ ሆነው አልተገኙም በሚል ስሞታ አንስተዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አዜብ መስፍን የሰበታ ከተማ ሰራተኞችን አሰረች

የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ባለቤት እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ “ወይዘሮ ሙስና” የሚል ቅጽል ስም የወጣላት አዜብ መስፍን ወደ ሰበታ ከተማ ሄዳ በርካታ የከተማ አስተዳደሩን ሰራተኞች በግል እንዳሳሰረች ለግንቦት 7 የደረሰ መረጃ አመልክቷል።

በደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን የምትገኘው የሰበታ ከተማ መስተዳደር፥ ከአየር በአየር የመሬት ንግድ ጋር በተያያዘ በከፍተኛ ደረጃ በሙስና ውስጥ የተዘፈቀ እንደሆነ እና አዜብ እራሷ በሺዎች የሚቆጠር ካሬ ሜትር መሬት በአካባቢው እንደተሰጣት ምንጮቻችን ጠቁመዋል። የከተማዋ የመሬት አስተዳደር ሰራተኞች ጉቦ እየተቀበሉ መሬት በማደል ከብረው አንዳንዶቹ በአስርተ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ብር እንዳካበቱ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ግለሰቦች ለግንቦት 7 ምንጮቻችን ተናግረዋል።

በተለይ በቅርብ ጊዜ ከአሜሪካን አገር የሄደ ግለሰብ፣ ጉቦ ሰጥቶ የግንባታ ስራ ለማከናወን በሚል አምስት መቶ ባለ አምስት መቶ ካሬ ሜትር መሬት መመራቱን፤ ነገር ግን ምንም ግንባታ ሳያከናውን መሬቱን በሙሉ ሸጦ ከአገር መውጣቱን ምንጮቻችን ገልጸዋል። በከተማዋ የነገሰው ሙስና አዜብን ጨምሮ በአገዛዙ ባለስልጣናት የታወቀ እንደነበረና፤ ከመሬት መስተዳደሩ መሃንዲሶች ውስጥ በተለይ አንዷ የአባ ዱላ ገመዳ የቀኝ እጅ እና የሙስና አቀናባሪ እንደነበረች ለማወቅ ተችሏል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የፓርቲ መዋቅሩን እያስፋፋ ነው ተባለ

ዘረኛው ገዢ ቡድን፣ መምህራን እና ተማሪዎችን የፓርቲ አባል እንዲሆኑ ማስገደዱ ሳያንስ፣ በተለይ የትምህርት ጥራትን እንደ ሽፋን በመጠቀም በትምህርት ቤቶች ውስጥ መዋቅሩን እያስፋፋ ነው ተባለ።

ለግንቦት 7 ድምጽ እና ለሌሎች መገናኛ ብዙሃን የተላከ መረጃ እንደሚያመለክተው፤ በየትምህርት ቤቶች ውስጥ ከተዘረጋው ዋና መዋቅር በተጨማሪ፣ መምህራን በህዋስ እንዲደራጁ እየተገደዱ ነው። በደቡብ ክልሉ የወያኔ ተለጣፊ ፓርቲ - ደኢህዴን - የተዘጋጀ እና “የአባል መምህራን ሞዴል ቅጽ” በሚል ርእስ የተዘጋጀ መመሪያ እንደሚለው፤ ድርጅቱ “በትምህርት ሴክተር የተደራጀ ሰራዊት ለመገንባት የሚያስችል መርሐ ግብር ዘርግቶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው”። ይሁን እንጂ የተቀረው የመመሪያው አካል መምህራን እንዴት አድርገው የትምህርት ጥራት ለማሻሻል መስራት እንደሚገባቸው ከማተት አልፎ፤ አባል መምህራን እና ተማሪዎች ሊፈርሙት የሚገባውን የስምምነት ቅጽ ያካትታል።
(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ከአገዛዙ የፍራፍሬ ድርጅት ብርትኳን እንዲገዙ እየተገደዱ ነው

"ኢት ፍሩት" የተባለው እና በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የመንግስት የፍራፍሬ ድርጅት፤ ሙዝ ብቻ ለመግዛት የሚፈልጉን የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ብርትኳንም እንዲገዙ እያስገደደ መሆኑን ከመዲናይቱ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ እንደሚያሳየው፥ የሙዝ ዋጋ ከብርትኳን ጋር ሲወዳደር ርካሽ በመሆኑ፣ አብዛኛው ነዋሪ ሙዝ ብቻ ሲገዛ በመስተዋሉ፤ ድርጅቱ ብርትኳን ለማይገዙ ተጠቃሚዎች ሙዝ አልሸጥም ብሎ ከልክሏል። ሙዝ በኪሎ ከ6-7 ብር ሲሆን፤ የብርትኳን ዋጋ የዛን እጥፍ እንደሆነ ታውቋል። ብርትኳን የተወደደበት ምክንያትም በአብዛኛው በአገዛዙ ቁጥጥር ስር ባሉ የመንግስት እርሻዎች ስለሚመረት ነው ተብሏል።

የግንቦት 7 ድምጽ ባለፈው አመት ባቀረበው ዘገባ፣ አንድ የኢትዮጵያ መከላከያ አውሮፕላን ብርትኳን ጭኖ በደቡብ ሱዳን ዋና ከተማ ወደሚገኝ የፍራፍሬ ነጋዴ መውሰዱን መዘገባችን ይታወሳል። የፍራፍሬ ነጋዴው በማይታወቅ ምክንያት ብርትኳኑን ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ፣ የአውሮፕላኑ አብራሪዎች በዋና ከተማዋ በጁባ መሃል ላይ ፍራፍሬውን አራግፈው ወደ ኢትዮጵያ መመለሳቸውን በወቅቱ የአይን እማኞች ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል። ፍራፍሬው የመጣው ከመንግስት እርሻ ሲሆን፤ ከሽያጩ በስተጀርባም የአገዛዙ ባለስልጣናት እንደነበሩበት ዘገባው ጠቅሶ ነበር።

# የትግራዩን ገዢ ጉጅሌ ከሥልጣን ማባረር ሃገራችንን ከድንቁርና ነፃ የማውጣት ትግል አካል ነው!!!

የሰለጠነ የሰው ኃይል ለልማት ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች ቀዳሚው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። የልማት ፍሬዓማነት መለኪያ ከሆኑ አመልካቾችም አንዱ የሰለጠነ የሰው ኃይል የመፍጠር አቅም መገንባቱ ነው።

ሃገር እንድትበለጽግ ከተመጽዋችነትና የበታችነት መንፈስ መላቀቅና በራስ የመተማመን ስሜት መገንባት ይገባል። በራስ የመተማመን ስሜት የሚገነባው ደግሞ የራስ የሆነን ነገር በማክበር እና የራስን አቅም በመገንባት ነው። ይህም ደግሞ የሰለጠነ የሰው ኃይል መገንባትን፤ የተገነባውን መንከባከብን እና በአግባቡ መጠቀምን ይጠይቃል።

በዛሬዋ ኢትዮጵያ እየሆነ ያለው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ኢትዮጵያዊውን ባለሙያ አያምንም። ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ወይም ምሁር በጉጅሌው ካድሬዎች የሚንጓጠጥ፣ የሚጉላላ፣ የሚሰደብና የሚረገጥ እንጂ በአገሩ ጉዳይ የሚናገር፤ ስለ አገሩ የሚቆረቆር መሆን አይችልም። ኢትዮጵያዊ ባለሙያና ምሁር የካድሬ መጫወቻ ነው። የትግራዩ ጉጅሌ በጉልበት ሥልጣን ከያዘበት እለት ጀምሮ በእውቀትና በአዋቂዎች ላይ ዘምቷል።

እውቀትንና አዋቂዎችን ከማጥፋት ጎን ለጎን ደግሞ የራሱን ትንሽነት መደበቂያ መንገድ ፈጥሯል። "እኔም የተማርኩና የተመራመርኩ ነኝ" በማለት የዝቅተኝነት መንፈሱን ለማስታመም ጉጅሌው ራሱን በግዢ በተገኙ የትምህርት ማስረጃዎች አንበሻብሿል። የሃገሪቱ የትምህርት ሥርዓትም እሱ ራሱ የያዛቸውን ዓይነት ባዶ ወረቀቶችን ማደያ አድርጎታል። በዚህም ምክንያት አገራችን ውስጥ ሙያም ባለሙያም ተዋርዷል። በዘመነ ወያኔ "የተማረ ነው" መባል የስድብ ያህል አሳፋሪ ሆኗል።

በእውቀትና በአዋቂዎች ላይ የተደረገው ዘመቻ ውጤት በየእለቱ እያየነው ነው:-

- ፍርድ ቤት ስንሄድ በስልክ እየተነገረው የሚፈርድ ዳኛ ችሎት ላይ ተኮፍሶ እናገኛለን፤
- የፍሳሽ ማውረጃ የሌላቸው ፎቆችን እየገነባ ያለ መሃንዲስ በጥበቡ ብዛት ይራቀቅብናል፤
- መርፌ በወጉ የማይወጉ ሃኪሞች በበሽተኞች ላይ ይዘባበናሉ፤
- ለተማሪዎቻቸው የሰጡትን ፈተና እራሳቸው ቢፈተኑ የማያልፉ መምህራን "ከኔ ባላይ ላሳር" ሲሉ ይገኛሉ።

በእንዲህ ዓይነት "የተማረ" ሰው ኃይል እድገት ሊመጣ ቀርቶ አሉበት መቆየትም አዳጋች ነገር ነው።

በአንፃሩ ቀድሞ የነበረው የትምህርት ሥርዓት በርካታ ድክመቶች የነበሩበት ቢሆንም በሙያቸው የተከበሩ ጥቂት ምሁራንን አፍርቷል። የመጀመሪያው አፍሪቃዊ አይሮፕላን አብራሪ፣ የመጀመሪያው አፍሪቃዊ የስልክ ቴክኖሎጂ ባለሙያ፣ የመጀመሪያዎቹ አፍሪካዊያን የስነ-መንግሥት ምሁራን ኢትዮጵያዊያን ነበሩ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ብቻ ሳይሆን በቴክኒክ ኮሌጅ የሚሰጡ ትምህርቶች በሰለጠኑ አገሮች ከሚገኙ ተቋማት ጋር መሳ ለመሳ የሆነ ተቀባይነት ነበራቸው። ምሩቃኑም ሙያ ብቻ ሳይሆን የአገር ፍቅር ስሜት የተላበሱ ነበሩ። እነማንዴላን ጨምሮ ኢትዮጵያ ለብዙ አፍሪካዊያን አርዓያ ነበረች። አሁንም ቢሆን የዚያ ወቅት አሻራ ያረፈባቸው ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች አሉ። እነዚህ ባለሙያዎች የሚገኙት ግን አሜሪካና አውሮፓ እና ሌሎች አገሮች ውስጥ እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ አይደለም። ሙያቸውን ጠንቅቀው ያወቁ፤ በራሳቸው የሚተማመኑ ባለሙያዎች ሁሉ ተገፍተው አገር ለቀው እንዲሰደዱ በመደረጋቸው ኢትዮጵያ ልትመካባቸው የሚገቡ ባለሙያዎች የሚገኙት በውጭ አገራት ውስጥ ነው።

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በየክልሉ ለህንፃዎች የዩኒቨርስቲነት ስያሜ መስጠቱን እናውቃለን። ወደ እነዚህ ህንፃዎች የሚመላለሰውም ወጣት ቁጥር በብዙ መጨመሩ እውነት ነው። ሆኖም ባለሙያ ሲያፈሩ ግን አልታዩም፤ ለዚህ ተግባር የተፈጠሩም አይደሉም።

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ያለበትን የእውቀት ማነስ የህዝብ ንብረት ለመሸጥ በምክንያትነት ሲያቀርብ መስማት ደግሞ ሌላው አስገራሚ ነገር ነው። ለምሳሌ:

- መሬትን በገፍ ለመሸጥ የሚያቀርበው ምክንያት "ግብርናውን የማዘመን አቅምም ችሎታም የለንም" የሚለው እንደሆነ ልብ ይሏል። "ኢትዮጵያዊያን የግብርና ባለሙያዎች የት ገቡ?" ብሎ መጠየቅ አይቻልም። እንዲያም ሆኖ ግን "የግብርና ባለሙያዎችን በገፍ እያሰለጠንኩ ነው" እያለ ይቦተልካል።
- "የማዕድን ሃብታችን ለማልማት የሚጠይቀው እውቀትና አቅም የለንም" የሚለው ሰበብም ቱጃሩን እየጠቀመ እንደሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ዛሬ የአገራችን የወርቅ ማዕድን በቱጃሩ ግለሰብ እጅ ውስጥ ገብቷል።
- አሁን ደግሞ "የማኔጅመንት ባለሙያ የለንም" በሚል ሰበብ ኮርፖሬሽኖችን መሸጥ ተጀምሯል። የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ማኔጅመንት ለፈረንሳይ ኩባንያ መሰጠቱ በመሬት የተጀመረው ሽያጭ ወደ ኩባንያዎች የመምጣቱ መርዶ ነጋሪ ነው። የሚቀጥሉት ተረኞች የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እና የኤለክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እንደሚሆኑ መጠበቅ ይቻላል።

ግንቦት7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህ በድንቁርናው በመኮፈስ ላይ ያለው፤ ፀረ-እውቀት እና ፀረ-አዋቂ የሆነው የትግራዩን አምባገነን ገዢ ካሰፈነብን የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ነፃ እስካልወጣን ድረስ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ሊኖር ይችላል ብሎ አያምንም። ስለሆነም የትግራዩን አምባገነን ገዢ ጉጅሌ በጋራ አስወግደን ሃገራችን ከገባችበት የድንቁርና አዘቅት እናውጣ እንላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## የዘረኛው አገዛዝ ካድሬዎች በተለያዩ ከተሞች የመሬት ቅሚያ መጀመራቸው ታውቋል

ለአመታት የመሬት ባለቤት ሆነው የቆዩ ዜጎች በህገ-ወጥ መንገድ ንብረቶቻቸውን እየተቀሙ ነው ሲል የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ ገልጿል።

የሻሸመኔ ከተማ መስተዳደር ሰራተኞች ወደ 60 ከሚጠጉ አባወራዎች መሬቶችን መቀማታቸው ታውቋል። ባለንብረቶቹ፥ መሬቶቹን የዛሬ ሃያ አመት ገደማ በህጋዊ መንገድ ማግኘታቸውን እና ግንባታ ማካሄዳቸውን ይገልጻሉ። አንዳንድ ምንጮች የመስተዳደሩ ሰራተኞች መሬቶቹን ከዘመድ እና ጓደኞቻቸው ጋር መከፋፈላቸውን ይናገራሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ፥ በአዲስ አበባ ከተማም ካድሬዎች እና የህግ አስከባሪ ተቋማት አባላት በመመሳጠር ዜጎችን ለረዥም አመታት ከኖሩባቸው ቤቶች እያባረሩ እና በህገ-ወጥ መንገድ የሌሎችን ንብረቶች ወደራሳቸው ስም እያስተላለፉ መሆኑን ምንጮቻችን ገልጸዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ የመሬት ባለቤትነት መዝገብ አያያዝ እጅግ ደካማ መሆኑ ለአገዛዙ ካድሬዎች የዘረፋ እድል ፈጥሯል ሲሉ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ግለሰብ ገልጸዋል።

ዘጋቢያችንን ያናገሩ አንድ የምእራብ ኢትዮጵያ ከተማ ነዋሪ፣ ከመሬት ጋር በተያያዘ ወያኔ በህዝቡ ላይ የዘረፋ ብቻ ሳይሆን የበቀል እርምጃም እየወሰደ ነው ብለዋል። አንዳንድ በሃይለስላሴ ዘመን መሬት ገዝተው የመኖሪያ ቤቶቻቸውን የገነቡ እና ካርታ ያላቸው ግለሰቦች ሳይቀሩ፤ ከአገዛዙ ካድሬዎች ጋር ቅርበት ስለሌላቸው ቤታቸውን የገነቡበት መሬት የነሱ እንዳልሆነ እየተነገራቸው መሆኑን መስክረዋል።

## የኦሮሞ ነፃነት ግንባር 53 የወያኔ ወታደሮችን መግደሉን ገለጸ

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር - ኦነግ - ባወጣው መግለጫ፣ 53 የወያኔ ወታደሮችን መግደሉን እና 38 ማቁሰሉን ገልጿል።

በህዳር ወር ውስጥ በሁለት የተለያዩ ቀናት በዘረኛው አገዛዝ ጦር ላይ ባደረሰው ጥቃት፤ በምእራብ ሐረርጌ 22 ገደሎ 23 ሲያቆስል፤ በባሌ 31 ገደሎ 15 ማቁሰሉን የድርጅቱ መገናኛ ብዙሃን ገልጿል። በምእራብ ሐረርጌ ጥቃቱን ሲፈጽም አንድ የወያኔ የጦር ካምፕ ለበርካታ ሰዓታት ተቆጣጥሮ መቆየቱንም አክሏል።

## የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት አመራር . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የዋሆች የታጠረ እንደመሆኑ በፖለቲካና ሌላም ጉዳዮች በቁጥጥር ሥር በዋሉ እስረኞች ላይ የሚፈጸመው ሰቆቃ በምንም መንገድ ለውጪ ሰው እንዲታወቅ አንደማይደረግና ሰቆቃ ፈጻሚዎች ምንም አይነት ተጠያቂነት እንደሌለባቸው ለማወቅ ተችሎአል።

የመረጃው አቀባዮች እንደሚሉት፣ በእስረኞች ላይ ከፍተኛ ድብደባን መፈጸም የተለመደ ተግባር ሲሆን፤ በድብደባው ብዛት የሞቱ፣ አካለ ጎደሎ የሆኑ እና ለአእምሮ በሽታ የተዳረጉትን ለመቁጠር ያዳግታል። በርካታ እስረኞችም ያለ ክስ በጨለማ ቤቶች ውስጥ ታጉረው የሚገኙ ሲሆን፤ በድብደባ የቆሰሉት ሆስፒታል ሄደው እንዳይታከሙ እና በቤተሰብ እንዳይጎበኙ ተከልክለዋል።

ዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ስልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ እንዲህ ያለ ግፍ ሲፈጽም መቆየቱ በውጭ እና አገር በቀል የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች በየአመቱ እንደሚመዘገብ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በመረጃ እጥረት ምክንያት እንዲህ አይነቱ ወንጀል የሚካሄድበትን ከፍተኛ ደረጃ ለማጋለጥ አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል።

መረጃ ማግኘትን አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ውስጥ አንዱም፣ የመንግስት ተቋማት በዋነኛነት የሚመሩት በችሎታቸው ህዝብን እንዲያገለግሉ በተቀጠሩ ታማኝ ዜጎች ሳይሆን በጎጥ በተዋቀሩ እና ለገዢው የማፊያ ቡድን እና ለራሳቸው ጥቅም ታማኝ በሆኑ ዘረኞች በመሆኑ እንደሆነ ከቅርብ አመታት ወዲህ እየወጡ ያሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

## የወያኔ አገዛዝ በአራት የትጥቅ ቡድኖች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

መግለጫው ለጥምረቱ መመስረት የኤርትራን መንግስት የሚወነጅል ሲሆን፤ "ይህ የህዝቦቻቸው በዘረኛው አገዛዝ መገፋት እና መታፈን በቅቷቸው ወያኔን ለመዋጋት የተነሱ በርካታ ኢትዮጵያውያን ቡድኖች መኖራቸውን ለመካድ አገዛዙ የሚያደርገው ሙከራ አካል ነው" ሲሉ አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል።

እኒሁ ግለሰብ ጨምረውም፥ የወያኔ አገዛዝ እውነት መግለጫው እንደሚለው ቡድኖቹ የሞቱ ናቸው ብሎ ቢያምን እንደዚህ ቁጣ በተሞላበት መልኩ፤ ታላቅ ቀውስ የተከሰተ ይመስል ረዥም መግለጫ ባላወጣ ነበር ብለዋል። መግለጫው፥ በአገዛዙ ላይ ያለው ስር የሰደደ አለመረጋጋት ስሜት ነጸብራቅ ነውም ሲሉ አብራርተዋል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## ትግሉ የኛ ድሉም የኛ ነዉ (ከኤፍሬም ማደቦ)

የአገራቸዉ የኢትዮጵያ በግፍ መወረርና የህዝባቸዉ በጋዝ መርዝ መጨፍጨፍ እጅግ ያሳሰባቸዉ ቀዳማዊ ኃ/ሥለሤ ጀኔቫ ድረስ ተጉዘዉ ለሊግ ኦፍ ኔሺንስ አቤቱታቸዉን ሲያሰሙ ቀን የማይደርስ መስሏቸዉ የግርማዊነታቸዉን አቤቱታ ካንቋሸሹት አገሮች ዉስጥ እንግሊዝና ፈረንሳይ ዋና ዋናዎቹ እንደነበሩ ታሪክ በሚገባ ዘክሮታል። እነዚህ ሁለት አገሮች አባቶቻችን በጋዝ መርዝ ሲቃጠሉ ማፌዛቸዉ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ እራሷን እንዳትከላከል የመሳሪያ ሺያጭ እገዳ ማድረጋቸዉና የኋላ ኋላ ከናዚ ጎን ተሰልፎ እነሱኑ ካስጨነቀ ኃይል ጎን መሰለፋቸዉ ታሪክ በቆሻሻነቱ የሚዘክረዉ ዘግናኝ ታሪክ ነዉ። ምዕራባዉያኑ መንግስታት መሳሪያ ሸጡም አልሸጡ ከ1928 ዓም እስከ 1933 ዓም ድረስ በነበሩት 5 የአርበኝነት አመታት ጀግኖች አባቶቻችን ለነፃነታቸዉ ሲታገሉ እንግሊዝ፤ ፈረንሳይና አሜሪካ ከጣሊያን ወራራ ያድኑናል ብለዉ ከትግላቸዉ የተዘናጉበት አንድም ወቅት አልነበረም። ይልቁንም የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ነፃነት አደራ የወደቀዉ እነሱ ጀርባ ላይ መሆኑን አዉቀዉ የፋሺስት ጣሊያንን የመሳሪያ ጋጋታ ከምንም ሳይቆጥሩ ጣሊያንንና አብሮት የተሰለፈዉን የባንዳ ኃይል አይቀጡ ቅጣት ቀጥተዋል።

የሚገርመዉ ቀዳማዊ ኃ/ሥለሤ ጀኔቫ ሄደዉ አገሬን አትርሷት ብለዉ ልዕለ ኃያላኑን ሲማፀኑ መልሳቸዉ ሸሙጥና ፌዝ የነበረዉ እንግሊዞች የኋላ ኋላ ኢትዮጵያን የረዱት ለኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት አስበዉ ወይም ሰብአዊነት ተሰምቷቸዉ ሳይሆን ከሂትለር ጎን የተሰለፈችዉንና የአንድ ወቀት አጋራቸዉን ጣሊያንን ለመበቀል ሲሉ ነዉ። ዛሬ 2ኛዉ የአለም ጦርነት በተባበሩት ኃይሎች ድል አድራጊነት ከተፈፀመ ከ64 አመታት በኋላ እንግሊዝ፤ጣሊያን፤ፈረንሳይና ጀርመን ከሌሎች 23 አገሮች ጋር የአዉሮፓን ህብረት ፈጥረዉ ወደ ዉህደት እየተጓዙ ነዉ።ሆኖም ከዚያ እንደ ሳምባ ምች ክፉኛ ካጠናፈራቸዉ የክህደት በሽታ ዛሬም ያገገሙ አይመስልም። የጣሊያን ፋሺስቶች አገራችንን ሲቀራመቱ ከወራሪዉ ኃይል ጎን የቆሙት እነዚህ አገሮች ዛሬም አገራችንን በዘርና በቋንቋ ከፋፍሎ ጥሬ ሃብቷን ከሚቦጠቡጥ የአገር ዉስጥ ቅኝ ገዢ ጎን ቆመዋል። በተለይ እንግሊዝና የአዉሮፓዉ ህብረት በታሪክ ጠንቅቀዉ የሚያዉቁትን የኢትዮጵያ ህዝብ ተረግጠህም ቢሆን በልተህ አስካደርክ ድረስ መብትህና ነፃነትህ ቀስ ብሎ ይከበርልሃል ማለታቸዉ እነዚህ ኃይሎች የእነሱ ጥቅም አስከተከበረ ድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነፃነት ደንታ እንደሌላቸዉ በግልፅ ያሳያል።

ስለምዕራቡ አለም የፖለቲካ ወላዋይነት ብዙም ግንዛቤ ያልነበራቸዉ አባቶቻቸን በየጫካዉ ገብተዉ ጠላትን ሲታገሉ ምዕራባዉያን ነፃ ያወጡናል የሚል ህልሙም ቅዠቱም አልነበራቸዉም። ዛሬ በመረጃ ዘመን የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ ደግሞ ምዕራባዉያንም ሆኑ ሌሎች አገሮች ከኢትዮጵያ ምን እንደሚፈልጉና ኢትዮጵያን ለምን እንደሚፈልጓት ጠንቅቆ ያዉቃል፤ ምዕራባዉያን ከእነሱ የኤኮኖሚና የፖለቲካ ፍለጎት ጋር እስካልገጠመ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብ የፍትህ፤የነፃነትና የዲሞክራሲ ጥያቄ ቢመለስ ባይመለስ ጉዳያቸዉ አይደለም። እንዳዉም እንደነሱ አባባል ነፃነት፤ ሰብዓዊ መብትና ዲሞክራሲ እንደ ሰዉ ልጆች መሠረታዊ እሴቶች የሚታዩት አዉሮፓና አሜሪካ ከዚያም ካለፈ በእድገት ወደ ፊት በገፉት ጃፓንና አዉስትራሊያ ዉስጥ ነዉ እንጂ አፍሪካዉያን ሆዳቸዉ አስከሞላ ድረስ አነዚህ መሠረታዊ እሴቶች በሁለተኛና በሦስተኛ ደረጃ የሚታዩ ተራ ነገሮች ናቸዉ። በእርግጥ በምዕራቡ አለም መረገጣችንና መረሳታችን አንገብግቧቸዉ የሚጮሁልን አያሌ ተራማጅ ሀይሎች አሉ፤ ሆኖም የእነዚህ ሀይሎች መልካም አስተሳሰብ የሚያበረታታን እንጂ ትግላችንን የሚተካ መሆን የለበትም።

ዛሬ ለምለሙን የአገራችንን መሬት አርሰዉ የራሳቸዉን ህዘብ የሚቀልቡት ህንድ፤ቻይናና ሳዑዲ ናቸዉ። እነዚህ አገሮች አይናቸዉ ያረፈበትን መሬት ሁሉ በርካሽ ዋጋ የሚቸበችብላቸዉ ሰዉ እስካገኙ ድረስ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለአገር ደህንነትና ለብሔራዊ ጥቅም የሚቆረቆር መሪ እንዲኖር አይፈልጉም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ምዕራባዉያን ዶላር ባስታቀፉት ቁጥር ለነሱ ጥቅም የወንድሞቻችንን ህይወት የሚገብር መለስ ዜናዊን የመሰለ ግድ የለሽ መሪ ተነስቶ አገር ወዳድ የሆነ መሪ እንዲተካ ቅንጥት ታክል ፍላጎት የላቸዉም። እነዚህ ሁለት ሀቆች ቁልጭ አድርገዉ የሚያሳዩን የዘረኛዉን የመለስ ዜናዊን አምባገነን አገዛዝ አስወግዶ ኢትዮጵያን ከአደጋ የማደን ትግል የሚጀመረዉም የሚጠናቀቀዉም በኛ በኢትዮጵያዉያን ብቻ መሆኑን ነዉ።

በቅርቡ ጎረቤታችን የሆነዉ የኬንያ ህዝብ ህገ መንግስቱ የኬንያን ህዝብ ፍላጎትና የዲሞክራሲ እድገት ደረጃ በጠበቀ መልኩ እንዲሻሻል ግፊት አድርጎ አዎንታዊ መልስ ማግኘቱ የሚታወስ ነዉ። ከዚህ ጥቂት ቀደም ሲል ደግሞ የኬንያ ህዝብ በህብረት ቆሞ አምባገነኖች የቀሙትን ድምፀ ዉሳኔ በሀይል ማስከበሩ የሚዘነጋ አይደለም። ከዚሁ ከአፍሪካ ሳንወጣ የማዳጋስካር ህዝብ የእርሻ መሬቱ ለኮሪያ ነጋዴዎች ሲቸበቸብ አሻፈረኝ ብሎ በመነሳት ሺያጩ እንዲቆም አድርጓል። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የእርሻ መሬቱ ዶላር ይዞ ለመጣ የባዕድ ነጋዴ ሁሉ ሲሸጥ እጁን የፍጥኝ ታስሮ ተመልካች ሆኗል፤ በሌላ በኩል ደግሞ እሱ የመረጠዉ መሪ ሲታሰር እንጂ ሥልጣን ሲረከብ አይቶ አያዉቅም። የኬንያና የማዳጋስካር ህዝብ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ እንዲወጣ የታገለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ ለራሱ ነፃነትና ሰብዓዊ መብቶች መከበር ክንዱን አበርትቶ የማይታገልበት ምንም ምክንይት ያለ አይመስለንም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነቱን ከማንም ለምኖ አያዉቅም፤ ነፃነት የፈጣሪ ስጦታ ነዉና ማንም ይሰጠኛል ብሎ ጠብቆም አያዉቅም። ይህ አስተዋይ ህዝብ ነፃነት በግልሰብ ደረጃ የሚደሰትበት እንደማህበረሰብ ደግሞ በጋራ የሚንከባከበዉ ህዝባዊ ንብረት እንደሆነ አበክሮ ይገነዘባል። ዛሬ ድንበራችን ለባዕዳን ገፀ በረከት ሆኖ የቀረበዉ፤ የእርሻ መሬታችን ካለፍላጎታችን ለባዕዳን የሚቸበቸበዉ፤ አባቶቻችን በክብር ያንቀላፉበት ቦታ በግሬደር የሚታረሰዉና ገዳማቶቻችን መሳሪያ ባነገቱ ሰዎች የሚታመሱበት ዋናዉ ምክንያት እንደ ሰዉ የማይቆጥረን የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ነፃነታችንን በመሳሪያ አፈሙዝ ስለቀማን ብቻ ነዉ። እንግዲህ በእናት አገራችን ዉስጥ እንደ ሰዉ ተቆጥረን በነፃነት ለመኖር ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነዉ፤ እሱም ህዝባዊ ትግል ነዉ።

አገራችን ዉስጥ ያለዉ አገዛዝ ባዕዳን ተዋጋልን ብለዉ ሲጠይቁት ዬት ልዝመትላችሁ ብሎ የሚጠይቅ፤ መሬት ስጠን ሲሉት ደግሞ ምን ያክል ትፈልጋላችሁ የሚል ተጠያቂነትና ሐላፊነት የጎደለዉ አገዛዝ ነዉ። ይህንን አገዛዝ ከቀድሞዎቹ አምባገነን አገዛዞች ልዩ የሚያደርገዉ ዬኔ ነዉ ብሎ በጎጥ ያደራጀዉ ለህዝብና ለአገር የማይታዘዝ ልዩ ጦር ያለዉ መሆኑ ነዉ። ይህ በጎጥ የተደራጀ ጦር ደግሞ አጥፋ ሲባል ለማጥፋት እየዘመረ የሚሄድ ግደል ሲባል ደግሞ ለምን ልግደል ሳይሆን ስንት ልግደል የሚል እጅግ በጣም ጨካኝ የሆነ ጦር ነዉ። ይህ ጦርና ለዚህ ጦር ትዕዛዝ የሚሰጠዉ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ እስካሉ ድረስ ኢትዮጵያ ዉስጥ ነፃነት፤ ዲሞክራሲና እኩልነት የሚባሉ የሰዉ ዘር እሴቶች ሊኖሩ አይችሉም። አገራችን ኢትዮጵያን ይህንን ከመሰለ አሳፋሪ ዘረኛ ስርአት አላቅቆ በእኩልነት ላይ የተመሠረተች ኢትዮጵያን የመገንባት ግዴታ የኛ የኢትዮጵያዉያን በተለይም የዚህ ወጣት ትዉልድ ታሪካዊ ኃላፊነት ነዉ።

ዉሸት መታወቂያ ካርዱ የሆነዉ መለስ ዜናዊ "የኢትዮጵያን ህዝብ ከዲሞክራሲ ጋር አስተዋወቅነዉ" ብሎ ለአለም ህዝብ የተናገረዉ ከጫካ ወጥቶ አዲስ አበባን በረገጠ ማግስት ነበር፤ የሚገርመዉ ዛሬ ከሃያ አመታት በኋላ እንኳን የኢትዮጵያ ህዝብ የመለስ ዜናዊ የቅርብ ደጋፊዎችም ቢሆኑ ዲሞክራሲ ከደደቢት በረሃ እንደ ከላሺንኮቭ በመኪና ተጭኖ እንደማይመጣ በዉል ያወቁት ይመስላል። መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ የአንድ ፓርቲ አገር መሆኗን ሊነግረን ለምን 20 አመት እንዳስፈለገዉ ባናዉቅም ዛሬ ከሃያ አመታትና ከአራት አገራዊ ምርጫዎች በኋላ ኢትዮጵያ የአንድ ፓርቲ አገር የመሆኗ ነገር ግን ያለቀለት ጉዳይ ሆኗል። የሚገርመዉ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ በገዢዉ ፓርቲና በፓርላማዉ መካከል ካለዉ ልዩነት በዉኃና በበረዶ መካከል ያለዉ ልዩነት ይበልጣል። ለዚህ ነዉ ዛሬ መለስ ዜናዊና በዉጭዉ አለም ቀጥሮ ያሰማራቸዉ ተላላኪዎቹ ኢትዮዮጵያ የሚያስፈልጋት የኤኮኖሚ እድገት ነዉ እንጂ ነፃነትና ዲሞክራሲማ የተራበ ሰዉ አይቀልቡም እያሉ ለዘረኛዉ አገዛዝ ረጂም እድሜ የሚመኙት። ኢትዮጵያ ዉስጥ እድገት የሚባል ነገር ቢኖር ኖሮ የኢትዮጵያ ህዝብ ጨዉ ለመግዛት ዕቁብ መግባት አይኖርበትም ነበር፤ እነ መለስ ዜናዊ እድገት እያሉ የሚጮሁብን ጩኸት እዉነት ቢሆን ኖሮ አዲስ አበባ ዉስጥ ተማሪዎች ረሃብ እያጥወለወላቸዉ የሚማሩበት ክፍል ዉስጥ አይወድቁም ነበር። በ10 እና በ 11 በመቶ አደገ የተባለዉ ኤኮኖሚ እዉነትም በዚህ ስሌት አድጎ ቢሆን ኖሮ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ዉስጥ ምግብ በእጅ ጉርሻ እየተለካ አይሸጥም ነበር።

መለስ ዜናዊና የበረሃ ጓደኞቹ የባለስልጣን ቱጃር ያደረጋቸዉን መጠነ ሰፊ ዶላር በኢትዮጵያ ህዝብ ስም ካልሆነ በሌላ በማንም ስም እንደማያገኙት ጠንቅቀዉ ያዉቃሉ፤ ስለዚህ የሚጠሩበት ስም በትክክል እንደሚያመለክተዉ እነሱ የሚወክሉት አንድን አካባቢ ብቻ በመሆኑ ተቀዳሚ አላማቸዉ ኢትዮጵያን እንደ ፈረንጅ ላም እያለቡ የኛ ነዉ የሚሉትን አካባቢ ማልማት ነዉ። እነሱ እደገትና ልማት የሚሉትም ይህንኑ የተወለዱበትን አካባቢ እድገትና ልማት ነዉ።

መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ አዲስ አበባ ሲገቡ ሦስትና አራት አመት ዕድሜ የነበራቸዉ ልጆች ዛሬ ኮሌጅ ጨርሰዉ ወይ አለፍላጎታቸዉ የወያኔ አባል ሆነዋል አለዚያም የኛ አይደላችሁም ተብለዉ በወጣትነታቸዉ እንደ አሮጌ ዕቃ ተጥለዋል። እዚህ ላይ እጅግ የሚያሳዝነን ነገር ቢኖር አማራጭ አጥቶ የወየነዉም ሆነ ጎመን በጤና ብሎ ስራ አጥነቱን የመረጠዉ ኢትዮጵያዊ ወጣት ተስፋ የቆረጠና ፊት ለፊቱ የሚጠብቀዉን የብሩህ ዘመን መምጣት የሚጠራጠር ወጣት ነዉ። እዚህ ላይ ይህ ግፈኛ ስርአትም ሆነ የስርአቱ ደጋፊዎች ሊያዉቁት የሚገባ አንድ ሐቅ አለ። ተስፋ መቁረጥ ሰዎችን ወደበለጠ ተስፋ መቁረጥ የሚገፋፋ አደገኛ በሽታ ነዉ፤ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉም ነገሩ ተሟጥጦ አልቆ አንድ የቀረዉ ነገር ቢኖር ልጆቼ ከዛሬ ነገ ይደርሱልኛል የሚል ተስፋ ብቻ ነዉ። ይህንን ህዝባዊ ተስፋ በጠመንጃ አፈሙዝ ለማጨለም መሞከርና በእድገት ስም ህዝብን በአዝጋሚ ረሃብ መፍጀት ተነጣጥለዉ የሚታዩ ነገሮች አይደሉም። አንድን ህዝብ ወደ ጦርነትና ወደ እልቂት የሚወስደዉ የሰዎች በረሃብ መሞት ሳይሆን የተስፋ መሞት መሆኑን ታሪክ በብዙ መረጃዎች ያስገነዝበናል።

በዛሬዋ ኢትዮጵያ ዉስጥ ስራ ለማግኘት፤ ለመሾም፤ለመሸለም፤የንግድ ስራ ፈቃድ ለማግኘትና ዉጭ አገር ሄዶ ለመማር የወያኔ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ትግሉ የኛ ድሉም የኛ ነዉ . . . (ከገጽ 3 የዞረ)

ድርጅቶች አባል መሆን የግድ ነዉ። በእርግጥ የኢትዮጵያ ህዝብ እድሜ ልኩን ከብዝበዛና ከጭቆና ተላቅቆ አያዉቀም፡ ሆኖም እንደ መለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢትዮጵያን ህዝብ ክብር የረገጠ፤ህልዉናዉን ያንቋሸሸና ማንነቱን የደፈረ አገዛዝ አገራችን አይታ አታዉቅም። ባህር ተሻግረዉ የመጡ ቅኝ ገዢዎችን አይቀጡ አቀጣጥ የቀጣዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ እጅግ በጣም አናሳ ለሆኑ የአገር ዉስጥ ቅኝ ገዢዎች ሰጥ ለጥ ብሎ የሚገዛበት ምንም ምክንያት የለም።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ አገራችንን ኢትዮጵያንና ህዝቧን ምን ያክል እንደናቀ በግልፅ ከሚያሳዩን ብዙ ነገሮች አንዱ ሻምበል አበበ ቢቂላን የመሳሰሉ የአገር ክብርና ተምሳሌት የሆኑ ጀግኖች በክብር ያረፉበትን የቅዱስ ዮሴፍ መካነ መቃብር አፈራርሶ የስግብግቦቹ የወያኔ ሹማምንት የገንዘብ መሰብሰቢያ ቦታ ማድረጉ ነዉ። ይህ በቃኝን የማያወቅ ስግብግብነትና ማን አለብኝነት የሚያሳየን መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ገንዘብ እስካስገኘላቸዉ ደረስ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የማይፈጽሙት ምንም አይነት ወንጀል አለመኖሩን ነዉ። ይህ ደሞ በግልጽ የሚታይ አዉነት ነዉና ብዙ ማስረጃ የሚያስፈልገዉ አይመስለንም - በድንበራችን ጉዳይ ከጠላቶቻችን ጋር ተዋዉለዋል፤የአገራችንን ገበሬ መሬት ለባዕዳን ሸጠዋል፤ነፍስ ያለወቁ ህፃናት ልጆቻችንን በጉዲፈቻ ስም እንደ ዕቃ ሸጠዋል። እንደዚህ አይነቱ ቅጥ ያጣ ንቀት "ማን ይነካኛል" ወይም "ምን አባታቸዉ" ይሆናሉ ከሚል እብሪትና ጀብደኝነት የመነጨ ነዉ፤ ስለሆነም ከዚህ አይነቱ ዉርደትና ንቀት አንዱኑ የማይቀረዉ ሞት ይሻላልና የኢትዮጵያ ህዝብ እየሞተም ቢሆን ከዚህ አሳፋሪ የመከራ ኑሮ እራሱን ነፃ ማዉጣት አለበት።

በነፃነቱና በአንድነቱ ኮርቶ የሚኖር ህዝብ ታሪካዊ ማንነት የሚለካዉ የኩራቱ ምልክት የሆኑትን ነፃነትና የአገር አንድነት ለልጅ ልጆቹ ማስተላለፍ በመቻሉ ነዉ።በዛሬዋ ህገ ወጥነትና ዘረኝነት በነገሰባት ኢትዮጵያ የሚኖረዉ ኢትዮጵያአዊ ግን የሚጠበቅበት ይህ ቅዱስ አባታዊ አደራ ሳይሆን እራሱን ከአገር ዉስጥ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ማዉጣትና አገሩን ከተደቀነባት አደጋ ማዳን ነዉ።ደጋግመን እንደ ተናገርነዉ ነፃነት ማንም ቆርሶና ለክቶ ሊሰጠዉ የማይችል የህዝብ ንብረት ነዉ፤ ሆኖም ዛሬ በነፃነታቸዉ ኮርተዉ የሚኖሩ ህዝቦች ነፃነታቸዉን የተጎናፀፉት በመራራ ትግልና በመስዋዕትነት ነዉ እንጂ እጅ በመንሳት ወይም በልመና አይደለም። ዛሬ በወያኔ አፈሙዝ ታጥሮ በገዛ አገሩ በግዞት የሚኖረዉ የኢትዮጵያ ህዝብም ቢሆን ከዚህ ወያኔ ከጫነበት መከራ፤ስቃይ፤ ዉርደትና ንቀት እራሱን ነፃ ለማዉጣት ያለዉ ብቸኛ አማራጭ ህዝባዊ ትግል ብቻ ነዉ። በዚህ ለመብታችንና ለነፃነታችን በምናርገዉ የሞት የሽረት ትግል ዉስጥ ዘረኞች አንዳንዶቻችንን ሊያስሩ ሌሎቻችንን ደግሞ ሊገድሉ ይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን የማያዉቋትን እዉነትን፤ የሚረግጧትን ፍትህንና ከሁሉም በላይ ደግሞ በነፃነት የመኖር ፅኑ ፍለጎታችንን በፍፁም ሊገድሉ አይችሉምና ያለ ጥርጥር እናሸንፋለን።

## የአማራ ክልል ገበሬዎች በትምህርት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በአሁኑ ሰዓት ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት መላክ ጊዜ ማባከን በመሆኑም እቤት ቀርተው ከብቶች ቢጠብቁ እና እርሻ ቢያርሱ እንደሚሻላቸው ለባለስልጣናቱ ነግረዋል። አንዳንድ ገበሬዎች በወያኔ አገዛዝ ስር ባለው የትምህርት ጥራት ዝቅተኛነት ላይ ያላቸውን ንቀት ሲገልጹም፥ እንኳን ተማሪዎቹ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መምህራን እየሆኑ የሚመደቡት ወጣቶች እራሳቸው የመንግስት ማመልከቻ ጻፉልን ብለን ጠይቀን ባግባቡ ሊከውኑት አልቻሉም ሲሉ አውግዘዋል።

በዘረኛው አገዛዝ ስር ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ምሁራን በየአመቱ አገራቸውን ጥለው እንደሚሰደዱ እና የትምህርት ጥራት እጅግ ከመውረዱ የተነሳ በርካታ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን አንዳንድ ቅጾችን በአግባብ መሙላት እንደማይችሉ ይነገራል።

## አዜብ መስፍን የሰበታ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ይሁን እንጂ፥ የአሜሪካን አገሩ ግለሰብ ጉዳይ በባለስልጣናቱ ዘንድ ቁጣን የቀሰቀሰ ሲሆን፤ አንዱ ቱባ ባለስልጣን "ተላጥን" ሲል ተሰምቷል። ይህ በእንዲህ እንዳለም በርካቶቹ የከተማዋ የመሬት አስተዳደር ሰራተኞች የስራ መልቀቂያ ያስገቡ ሲሆን፤ ሁለቱ አገር ጥለው ለመውጣት ሲሞክሩ ቦሌ አየር ማረፊያ ላይ ተይዘዋል። ከቁጥጥሯ ውጪ የሆነ ሰው ከሙስናው መጠቀሙ ያናደዳት አዜብ መስፍንም፤ በግል ወደ ሰበታ ከተማ ሄዳ የተቀሩትን አስለቅማ ማሳሰሯ ታውቋል።

አዜብ የፓርላማ አባል እና የህወሃት ማእከላዊ ኮሚቴ አባል ከመሆኗ በስተቀር በፖሊስ ሃይሉ ወይም በጸረ-ሙስና ኮሚሽን ውስጥ ምንም የታወቀ ስራ የላትም። በጉዳዩ ላይ ያናገርናቸው አስተያየት ሰጪ፥ ሴትየዋ አገሪቷን እንዳሻት ማሾሩን እንዳጠናከረችበት ያሳያል ብለዋል።

ጨምረውም፥ "አገዛዙ ሙስና እንዲካሄድ የሚፈቅደው የራሱን ባለስልጣናት ለመጥቀም እና ሰዎችን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ሆኖ ሳለ፤ እነዛ የሰበታ ከተማ ሰራተኞች ግን ገንዘባቸውን ከሰበሰቡ በኋላ ከቁጥጥሩ ለመውጣት መሞከራቸው ነው ስህተታቸው" ብለዋል። "እነ አዜብ የይለፍ ፈቃድ ላልሰጡት የዳያስፖራ ሰው ያን ያህል መሬት አንስተው መስጠታቸው ሳያንስ፤ ከአገር ለመውጣት መሞከራቸው ለሌሎች የአገዛዙ ካድሬዎች መጥፎ ምሳሌ ስለሆነ ከአሁኑ መቀጣጫ መደረግ ነበረባቸው" ሲሉም አብራርተዋል።

የአየር በአየር የመሬት ንግድ ከቁጥጥሩ መውጣቱን የተገነዘበው ወያኔ፤ አዲስ የመሬት አዋጅ እንዳወጣም ለማወቅ ተችሏል።

## የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ አፈና በኢትዮጵያውያን ላይ መበርታቱ የትጥቅ ቡድኖችን እያጠናከረ ነው ተባለ

በተለይ ከግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት በኋላ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከፓርላማው ውስጥ ፈጽሞ እንዲጠፉ መደረጉ የትጥቅ ቡድኖችን እያጠናከረ ነው ሲል ጅማ ታይምስ የተባለው የዜና ድረ-ገጽ ዘግቧል።

ድረ-ገጹ ሁለት የፖለቲካ ተንታኞችን በመጥቀስ፥ ህዝቡ፣ በተለይም ወጣቱ፣ በህጋዊ ትግል ያለውን እምነት በከፍተኛ ደረጃ እንዳጣ እና ይህም አገዛዙን ለመዋጋት ነፍጥ ያነሱ ቡድኖችን እየረዳ መሆኑን ዘግቧል። የፖለቲካ ተንታኞቹ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) እና የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንቅስቃሴዎቻቸውን መጨመራቸውን እንደ ማስረጃ ጠቅሰዋል።

ኦነግ በቅርቡ በወያኔ አገዛዝ ላይ ባካሄዳቸው ሁለት ጥቃቶች በአስርት የሚቆጠሩ ወታደሮችን መግደሉ እና በርካቶችን ማቁሰሉን እንደገለጸ መዘገባችን ይታወሳል። ኦብነግ ደግሞ ባለፉት በርካታ ወራት የተለያዩ ድሎችን ማስመዝገቡን ሲገልጽ የቆየ ሲሆን፤ ባለፈው ሳምንት 35 ወታደሮችን መግደሉን በመግለጫው አስታውቋል።

## በዜጎች አፈና የሚሳተፉ የወያኔ ባለስልጣናት ወደ አውሮፓ አገራት ከመግባት እንዲታገዱ የጀርመኑ ግሪን ፓርቲ ጥሪ አቀረበ

የጀርመን አገሩ ግሪን ፓርቲ ባወጣው የአቋም መግለጫ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚደርገውን ጥረት ለመደገፍ መወሰኑ ተዘግቧል።

ፓርቲው በመግለጫው፥ ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ የዛሬ ሃያ አመት ስልጣን ሲቆጣጠር ዴሞክራሲን አሰፍናለሁ ብሎ ቃል መግባቱ ሃሰት ሆኖ እንደተገኘ አስታውሶ፤ በኢትዮጵያ የሚፈጸመውን ግፍ እና አፈና ዘርዝሯል። ባለፈው አመት ግንቦት 15 ቀን የተካሄደው የምርጫ ተውኔት በነፃ እና ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ አለመካሄዱን እና በተቃዋሚ ቡድኖች ላይ ጥቃት ሲካሄድ መቆየቱን መስክሯል። የወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳን ለሁለት አመታት እስር ላይ መቆየት፤ የወ/ሮ አማረች ገላኔን እና የአቶ አረጋዊ ገብረዮሃንስን ግድያም እንደ ምሳሌ ጠቅሷል።

ዘረኛው እና አምባገነናዊው አገዛዝ በአገር ቤት ገለልተኛ መገናኛ ብዙሃንን ማስወገዱ ሳያንሰው፤ ከውጭ አገር የሚተላለፉ የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙሃንንም ማፈኑን ፓርቲው አውግዟል።

አለማቀፉ ማህበረሰብ በዚህ ጉዳይ ላይ ሲያሳይ የቆየው መቆጠብ ተቀባይነት እንደሌለው በመጥቀስ፤ ከዚህ በኋላ ዝምታው ሊያበቃ ይገባዋል ብሏል።

ግሪን ፓርቲ ይህንን አላማ ከግብ ከማድረስ አኳያ በርካታ የተግባር ውሳኔዎችን የደረደረ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ በሚካሄደው የሰብአዊ መብት ጥሰት እና አፈና ተሳታፊ የሆኑት ግለሰቦች ወደ አውሮፓ ህብረት እንዳይገቡ እና ገንዘባቸውም እንዲታገድ የህብረቱን አባል አገራት እንደሚጠይቅ ገልጿል። የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚፈጸሙት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ ምርመራ እንዲያካሄድ የጀርመን መንግስት ጫና እንዲያደርግም እጠይቃለሁ ብሏል።

የዝግጅት ክፍላችን በዚህ ጉዳይ ላይ ያነገራቸው አንድ የፖለቲካ ተንታኝ፥ ምንም እንኳ እንደዚህ ንቁ የሆኑ አንዳንድ የምእራባዉያን አገራት ቡድኖች እና ግለሰቦች ቢኖሩም፤ ነፃነታችንን ልናስከብር የምንችለው ግን እኛው እራሳችን መሆናችንን ለደቂቃ እንኳ መርሳት እና መዘናጋት የለብንም ብለዋል።

## ወያኔ በትምህርት ቤቶች ውስጥ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ለዝግጅት ክፍላችን መረጃውን ያቀበሉት ምንጭ፥ ይህ አገዛዝ መዋቅሩን ለማስፋፋት የሚጠቀመው ሽፋን ነው ብለዋል። ይህ ጉዳይ የወያኔ የፓርቲ ፖለቲካ ምን ያህል ትምህርት ቤቶቻችንን እና ማህበረሰባችንን እንደወረረ ያሳያል ያሉት ምንጭ፤ እነዚህ መዋቅሮች የተፈጠሩት የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ለመከፋፈል፣ ለስለላ ስራ እና ወደፊት ሊነሳ የሚችልን ተቃውሞ ለማፈን ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ገልጸዋል። "ሂውማን ራይትስ ዋች" በኢትዮጵያ ላይ በቅርቡ ባወጣው ሰፊ ሪፖርት፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ስለሚካሄደው የአፈና ስራ መዘርዘሩ ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**
ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org